The የፍሬገነት ፋውንዴሽን
Fregenet*foundation*
*Educating Needy Children for Success*

ሰኔ 30 ቀን 2001

ለ ጃኩሊን ሆልዘር እና ለበርናዴት ፖሽ
ማይ ቱ ሴንትስ ግብረሰናይ ድርጅት
ኦስትሪያ እና ሎስ አንጀለስ

የተወደዳችሁ ጃኩሊን እና በርናዴት

ለፍሬገነት ኪዳን ለህፃናት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ዩኒፎርም መርጃ ይሆን ዘንድ በሲ.ፈልድ ኦስትሪያ የሚገኙ ህፃናትን በማስተባበርና "ተማሪዎች ለተማሪዎች" የሚል የሩጫ ፕሮግራም በማዘጋጀት ወደ ሶስት ሺ.ህ ዶላር አሰባስባችሁ እርዳታ በመስጠታችሁ ከልብ የመነጨ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

የፍሬገነት ኪዳን ለህፃናት መላው የቦርድ አባላት ለተማሪዎቻችን ያደረጋችሁትን ድጋፍ ከልብ እያደነቀ በተሰጠው ድጎማም የፋውንዴሽኑን ዓላማ በማስፋፋትና በተግባር በመተርጎም በርካታ ህፃናትን ተቀብለን የትምህርትና ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶችን በሰፊው ለማዳረስ ጥረታችንን እንቀጥልበታለን።

ፋውንዴሽናችን በተጨማሪም ከማይ ቱ ሴንትስ ጋር የጀመረውን የውዳጅነት ትብብር የበለጠ በማጠናከር ዕርዳታ ለሚሹ በርካታ ህፃናት የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ እንቅስቃሴውን ወደ ላቀ ደረጃ እንደሚያሸጋግር በዚህ አጋጣሚ ያረጋግጥላችሁዋል።

ከዚህ በተጨማሪም ይህን የርዳታ ማሰባሰቢያ የተማሪዎች የሩጫ ፕሮግራም ያስተባበሩትን ትምህርት ቤቶችና መምህራን እንደዚሁም ወደ 500 የሚጠጉትን የሩጫ ተሳታፊ ተማሪዎችን በዚህ አጋጣሚ ከልብ እናመሰግናቸዋለን።

ስለ ፍሬገነት ፋውንዴሽን የሥራ እንቅስቃሴ የበለጠ ወቅታዊ መረጃ ማግኘት ከፈለጋችሁ www.fregenetfoundation.org ድረገጹን መመለከት እንደምትችሉ በትህትና እየገለጽን ለዚህ የተቀደሰ ዓላማና ወደፊት ለምናደርገው ቀጣይነት ያለው የሥራ ትብብር ምንግዜም ዝግጁነታችንን እናረጋግጥላችሁዋለን።

ላደረጋችሁልን ዕርዳታ በድጋሚ ከልብ እያመሰገንን፣ ለማናቸውም ጥያቄና የሥራ ግንኙነት በ 213-625-1867 ስልክ ቁጥር ደውሉልን።.

ከታላቅ አክብሮት ጋር,

ታፈስ ውብሸት
የፍሬ ገነት ፋውንዴሽን ፕሬዜዳንት

*123 S. Figueroa Street #1533 Los Angeles, CA 90012,* *Tel 213-625-1867*
*info@fregenetfoundation.org* *www.fregenetfoundation.org*